HM Government

Grenfell community updates

# Grenfell Tower community update: October 2025 - Amhraic / አማርኛ

**የግሬንፌል ታወር የማህበረሰብ ዝማኔ - ኦክቶበር 2025**

ግሬንፌል ታወርበአደጋው በጣም ለተጎዱት ሰዎች ጥልቅ ግላዊ ትርጉም እንዳለው እና መሬቱ ለቤተሰቦቹ የተቀደሰ እንደሆነ እንገነዘባለን። ታወሩን በጥንቃቄ የማፍረስ ስራችን አስመልክቶ ወቅታዊ መረጃ እንዲኖርዎት እንፈልጋለን።

በዚህ አዲስ መረጃ ውስጥ ስለሚከተሉት ተጨማሪ ማወቅ ይችላሉ፡-

- ስለ ጫጫታ፣ አቧራ እና ንዝረት መረጃን መከታተል
- ስለጤና እና ደህንነት
- እንዴት እኛን ማነጋገር እንደምትችሉ

ከዚህ ቀደም የነበሩትን ዝማኔዎች በሚከተለው ድረ-ገጽ ላይ መመልከት ይችላሉ፡- www.gov.uk/grenfell-community-updates

## ስለ ጫጫታ፣ አቧራ እና ንዝረት መረጃን መከታተል

መንግስት በግሬንፌል ታወር ጣቢያ ላይ የሚሰራው ሁሉም ስራ በከፍተኛ ጥራት መከናከወኑን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። የማህበረሰቡ እና በጣቢያው ላይ የሚሰሩ ሰዎች ጤና እና ጥበቃ ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው።

በሴፕቴምበር ወር ላይ የአየር ጥራት እና የጫጫታ ደረጃዎችን እንዴት እንደምንከታተል የሚያብራሩ ዝርዝር እቅዶችን አጋርተን ነበር። ስለእነዚህም ነገሮች ማንበብ እና እቅዶቹን በሚከተለው አድራሻ ማየት ይችላሉ፡-
ግሬንፌል ታወር፡- የማህበረሰብ ዝማኔ ሴፕቴምበር 2025 - GOV.UK

በታወሩ ጣቢያ ሶስት የንዝረት መቆጣጠሪያዎች እና አምስት የአየር ጥራት መቆጣጠሪያዎች ብሎም በጣቢያው ወሰን ዙሪያ ሶስት የጫጫታ መቆጣጠሪያዎች ያሉ ሲሆን ሁሉም የቀጥታ መረጃን ይሰበስባሉ።

እያደረግን ያለነው ስራ ተጽእኖ እርስዎ ይረዱ ዘንድ ከእነዚህ መቆጣጠሪያዎች የተገኘውን መረጃ እያጋራን እንገኛለን። ውሂቡ በመስፈርት የተቀመጡትን ደረጃዎች ካፉ እና ይህ ለምን እንደተከሰተ እና ስለ ጉዳዩ ምን እያደረግን እንደሆነ ያሳያል።

ይህንን ውሂብ በየወሩ እናትማለን። እያንዳንዱ ዝማኔ ከወሩ በፊት የነበሩትን ውጤቶች ያሳያል።

የቅርብ ጊዜዎቹ የጫጫታ፣ የአቧራ እና የንዝረት ክትትል ሪፖርቶች ከሴፕቴምበር 1 እስከ ሴፕቴምበር 28፣ 2025 ያሉ ናቸው።

የጫጫታ ክትትል ሪፖርት - ከሴፕቴምበር 1 እስከ ሴፕቴምበር 28፣ 2025

የአቧራ ክትትል ሪፖርት - ከሴፕቴምበር 1 እስከ ሴፕቴምበር 28፣ 2025

[የንዝረት ክትትል ሪፖርት - ከሴፕቴምበር 1 እስከ ሴፕቴምበር 28፣ 2025]

ከዚህ ባሻገር፣ የዩኬ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ (UK Health Security Agency, UKHSA) ስራ በሚከናወንበት ጊዜ በግሬንፌል ታወር አካባቢ ያለውን የአየር ጥራት መገምገሙን እና መከታተሉን ይቀጥላል። በየወሩ ሪፖርቶችን ማጋራታቸውን ይቀጥላሉ። የቅርብ ጊዜውን እዚህ ማንበብ ይችላሉ፦ [የግሬንፌል ታወር እሳትን ተከትሎ የአካባቢ ጥበቃ ክትትል - GOV.UKK]

**የጤና እና የጤንነት ድጋፍ ከፈለጉ**

ታወሩን በጥንቃቄ ለማፍረስ ስሜታዊ እና አካላዊ ደህንነት ድጋፍ ለሟች ቤተሰቦች፣ በሕይወት ለተረፉ እና በቅርብ ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች መደረጉን ቀጥሏል።

ከአንድ ሰው ጋር መነጋገር ከፈለግአችሁ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፦

- ወደ Grenfell Wellbeing አገልግሎት በ 020 8637 6279 (ከ8am እስከ 8pm፣ በየቀኑ) ይደውሉ።
- በድንገተኛ ጊዜ የማዕከላዊ እና የሰሜን ምዕራብ ለንደን የNHS ፋውንዴሽን ትረስት (Call Central and North West London, CNWL) ነጠላ የመድረሻ አማካሪ መስመርን በሚከተለው ቁጥር ይደውሉ፦ 0800 0234 650 (በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት ክፍት ነው)
- ኢሜል፦ grenfell.wellbeingservice@nhs.net
- ለተጨማሪ መረጃ: www.grenfellwellbeing.cnwl.nhs.uk ን ጎብኙ

ስለሚገኙ አገልግሎቶች የቅርብ ጊዜ መረጃ ለማግኘት፣ www.grenfell.nhs.ukን ይጎብኙ

**ከእኛ ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚችሉ ወይም የበለጠ ለማወቅ**

መረጃን ለእርስዎ ጠቃሚ በሆነ መንገድ ማጋራት እንፈልጋለን። በመጪዎቹ ወራት ውስጥ መደበኛ ዝማኔዎችን እና መረጃዎችን በ www.gov.uk/grenfell-community-updates ላይ ማጋራታችንን እንቀጥላለን እርስዎ ከፈለጉ፣ መደበኛ ዝማኔዎቻችንን በቀጥታ በኢሜይል መላክ እንችላለን።

ስለ ሥራው ለመወያየት፣ ስጋቶችን ለማጋራት እንዲሁም በመደበኛ ስብሰባዎቻችን ላይ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ባለስልጣናትን እና የእኛን ዋና ስራ ተቋራጭ ማነጋገር ይችላሉ። ለእርስዎ ለሚስማማ እና ምቹ በሆነ ሰዓት፣ ቀን እና ቦታ በግልም ሆነ በቡድን ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ ነን።

እባክዎን ከስራዎቹ ጋር የተያያዙ ማናቸውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት ወይም እኛን ለማነጋገር ማመቻቸት ከፈለጉ ያነጋግሩን። በኢሜይል ሊያነጋግሩን ይችላሉ፦ GrenfellTowerSite@communities.gov.uk

በግሬንፌል ታወር ላይ የቅርብ ጊዜ ዝማኔዎችን ለማግኘትና ለኢሜይል ማሳወቂያዎች ለመመዝገብ፣ እባክዎ ወደሚከተለው ድረገጽ ይሂዱ፦ www.gov.uk/grenfell-community-updates ወይም ከታች ያለውን የQR ኮድ ይቃኙ።

ለግሬንፌል ታወሩ አሳዛኝ አደጋ ምላሽ በመስጠት ስለምናደርገው ሥራችን ወቅታዊ መረጃዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚመርጡ ለማወቅ በቀጥታ ከእርስዎ መስማት እንፈልጋለን። ከፈለጉ፣ የእኛን ፈጣን የግብረመልስ ቅጽ በመሙላት የእርስዎን አስተያየት ማጋራት ይችላሉ፡-

[የግሬንፌል ማህበረሰብ፡- የግንኙነት ግብረመልስ ቅጽ - GOV.UK]